2715

# ብርሃነ ሕሊና ።

ለልዑል መኰንን መስፍን ሐረር
የተሰጠ ገጸ በረከት ።

ከልዑል መኰንን አሽከሮች አንዱ
ከበበደ ሚካኤል ተጻፈ ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም
በኢ ን ነገ መንግ መርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org



ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ።
መስፍነ ሐረር ።

www.ethiopianorthodox.org

## ልዑል ሆይ ፤

ይህንን መጽሐፍ ገጸ በረከት አድርጌ ለል ዑልነትዎ ለመስጠት አስቤ የጀመርኩት የዛሬ ስድስት ዓመት ነበረ ። አገራችን የጦር አደጋ ደርሶበት ልዑልነትዎ በስደት ምክንያት ወደ አውሮፓ ስለሔደ ጀምሬው የነበረውን በልዩ ልዩ ብስጭት ምክንያት ሁለት ዓመት ሙሉ ሳልቀጥል ተውኩት ። በኋላ ግን የኢትዮጵያ ነፃነት ለመመለሱ ያለን ተስፋ እየተረጋገጠ ስለሔደ የጀመርኩትን እንደገና ለመቀጠል ሐሳቤ ተነሣሣ ። ላሁኑ ሰዓት አድርሶኝ ልዑ ልነትዎ ከግርማዊ አባትዎ መንግሥት ለመመ ለስ በቅቶ ሐሳቤን ለመፈጸም የፈቀደልኝን ሕያው እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ ይህችን ትንሽ መጽሐፍ ለልዑልነትዎ በረከት አድርጌ አቀርባለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ያራት ዓመት ድካም የተለፋበት
ልዑል ሆይ እነሆ ገጸ በረከት ።

ይህ ገጸ በረከት ያቀረብኩልዎ
ይመልከተው ስል ነው ልዑልነትዎ ።

ለሚመረምራት ከጫፍ እስከ ስርዋ
ልዑል ሆይ ይች ዓለም ብዙ ነው ምግባርዋ ።

በብዙ ዓይነት አንጻር የታነጸው መልኳ
አብዝቶ ይታያል ጌጥን ያለ ልኳ ።

ይህ ሁሉ ያለም ጌጥ ሲያዩት ያማልላል
ውሥጡ ዕሬት ሆኖ ውጭው ማር ይመስላል ።

ዓለም ለሚወዳት እመቤቱ ናት
ንቆ ለሚያስተውላት ትዋረዳለች ።

ሰው አጭር ሕይወቱ ዋጋ እንድታገኝ
ለምንም አይበጅው ጨዋታን ቢመኝ ።

ሥጋም ወዳቂ ነው ገንዘብም ይረግፋል
ሀብትና ጌትነት ያለም ክብር ይጠፋል
ባለም ያለ ነገር ሁሉም አብሮ ያልፋል ።

መልካም ስም መመሥረት ደግ መሥራት ብቻ
ለዋጋው ሰፊነት የለውም ዳርቻ ።

ትክክለኛን ፍርድ የሌለውን መድሎ
እንደነ ሰሎሞን መስጠት አደላድሎ ።

መሥራትና መድከም መጣጣር ከልብ
ሰው ደስ ለማሰኘት ማሰብ በጥበብ
ተጣጥሮ መግዛት ፍቅርን ከሕዝብ ።

ምንም ብዙ ቢሆን የደስታ ዓይነቱ
የሚበልጠው ይህ ነው የተረፈው ከንቱ ።

ካባት ካያትዎ የመጣውን ቅርስ
ልዑልነትዎ ጥበብን ይውረስ ።

አብበ እሚታየው ከታደለው ዘር
መልካሙ ስምዎ ታድሶ ይኑር ።

www.ethiopianorthodox.org

ጌትነት ድህነት ጤንነት በሽታ
ተድላና መጉላላት መከራ ደስታ ።
ሰው ቢያጣ ቢጨነቅ ቢቸገር ቢያገኝ
ሰበብ ምክንያቱ ለሁሉ እኔ ነኝ ።
ከአዳም ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ
ደግና ክፉውን ጽፌ አጠራቅሜ ።
ስፈርድም መልሼ ደግሞ እንደማያውቅ
ምን ሠርተሃል ብዬ ኋላ እምጠይቅ ።
መልካሙን ሸልሜ ክፉን የምቀጣ
ሳልታይ ዓይቼ ሳልሄድ የምመጣ ።
በሰፊው ምሕረቴ በሌለው ወሰን
ሁል ጊዜ አድናለሁ የለመነኝን ።
መንግሥቴን ዘርግቼ ባለም በሰማይ
ጽድቅና ኃጥኔ በፍርድ የምለይ ።
ሳልጀምር ሳልጨርስ በክብሬ እምረጋ
እኔ ነኝ ዘለዓለም አልፋና ኦሜጋ ።

## የ ሰ ው ሐ ሳ ብ ።

አንድ ቀን ሐሳቤን ተከትዬ ስኼድ
ብዙ ጓደኞቼን አገኘሁ እመንገድ ።



እሩቅ አገር ያሉት አስቀድመው መጡ
ቀጥሎም የሞቱት ከጠፉበት ወጡ ።
ትክክል ተያይተን ተገናኝተን ደህና
ሁሉም አጠገቤ ተሰበሰቡና ።
ጥቂት ሳይለወጥ ወዝና መልካቸው
ሳይከሱ ሳይጠቁሩ ጥንት እንደማያቸው ።
ሰላምታ ሰጥተውኝ ሁሉም አንድነት
እየተነጋገርን ስንጨዋወት ።
በፍጹም አባክኖ ሐሳቤ አታሎኝ
እውነት ይኸ ሁሉ የሆነ መስሎኝ ።
ልቤ ተሸብሮ እየሳቀ ጥርሴ
በጣም ደስ ብሏት ስትጫወት ነፍሴ ።
ፈዞ የነበረው መንፈሴ ሲነቃ
ቤት ንብረታቸውን እየና ሲያበቃ ።
ትክ ብሎ አስተውሎ ቢመለከታቸው
ተርገበገበና መላ ቁመናቸው
እየተጣደፉ ባፈጣጠናቸው ።
ተፈትም ተኋላ ተቀኝም ተግራ
እየጠፉ ሔዱ በተራ በተራ ።
በዚህ የተነሣ ደንቆኝ እጅግ አርጎ
ጭራሹን ለማየት ይላል ቪክቶር ሂጎ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጌትነት ድህነት ጤንነት በሽታ
ተድላና መጉላላት መከራ ደስታ ፡፡
ሰው ቢያጣ ቢጨነቅ ቢቸገር ቢያገኝ
ሰበብ ምክንያቱ ለሁሉ እኔ ነኝ ፡፡
ከአዳም ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ
ደግና ክፉውን ጽፌ አጠራቅሜ ፡፡
ስፈርድም መልሼ ደግሞ እንደማያውቅ
ምን ሠርተሃል ብዬ ኋላ እምጠይቅ ፡፡
መልካሙን ሸልሜ ክፉን የምቀጣ
ሳልታይ ዓይቼ ሳልሄድ የምመጣ ፡፡
በሰፈው ምሕረቴ በሌለው ወሰን
ሁል ጊዜ አድናለሁ የለመነኝን ፡፡
መንግሥቴን ዘርግቼ ባለም በሰማይ
ጽድቅና ኀኔ በፍርድ የምለይ ፡፡
ሳልጀምር ሳልጨርስ በክብሬ እምረጋ
እኔ ነኝ ዘለዓለም አልፋና ኦሜጋ ፡፡

---

## የ ሰ ው  ሐ ሳ ብ ፡፡

አንድ ቀን ሐሳቤን ተከትዬ ስኼድ
ብዙ ጓደኞቼን አገኘሁ እመንገድ ፡፡



እሩቅ አገር ያሉት አስቀድመው መጡ
ቀጥሎም የሞቱት ከጠፉበት ወጡ ፡፡
ትክክል ተያይተን ተገናኝተን ደህና
ሁሉም አጠገቤ ተሰበሰቡና ፡፡
ጥቂት ሳይለወጥ ወዝና መልካቸው
ሳይከሱ ሳይጠቁሩ ጥንት እንደማያቸው ፡፡
ሰላምታ ሰጥተውኝ ሁሉም አንድነት
እየተነጋገርን ስንጨዋወት ፡፡
በፍጹም አበክኖ ሐሳቤ አታሎኝ
እውነት ይኸ ሁሉ የሆነ መስሎኝ ፡፡
ልቤ ተሸብሮ እየሳቀ ጥርሴ
በጣም ደስ ብሏት ስትጫወት ነፍሴ ፡፡
ፈዞ የነበረው መንፈሴ ሲነቃ
ቤት ንብረታቸውን እየና ሲያበቃ ፡፡
ትክ ብሎ አስተውሎ ቢመለከታቸው
ተርገበገበና መላ ቁመናቸው
እየተጣደፉ በፈጣጠናቸው ፡፡
ተፈትም ተኋላ ተቀኝም ተግራ
እየጠፉ ሔዱ በተራ በተራ ፡፡
በዚህ የተነሣ ደንቆኝ እጅግ አርጎ
ጭራሹን ለማየት ይላል ቪክቶር ሂጎ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ኀዘን የወረረው ገብቶኝ ብስጭት
ተጕሳቄለና ልቤ በጸጸት ።

ተነሣ መንፈሴ ገብቶ ሊመረምር
ከቶ ምን እንደሆን የሰው ሐሳብ ምሥጢር ።

አይቶና ተረድቶ ሊነግረኝ ውሥጡን
አሸዋ ወይ ድንጋይ ጭቃም እንደሆን ።

ከውሥጡ ያለውን ነገር ለማወቅ
ካሳቢ ባሕር ገብቶ መንፈሴ ቢጠልቅ ።

እጅግ የሚያስቸግር አገኘው ሁከት
በዚያም በዚህ ቢዞር በየኼደበት
የሚያገኘው ሁሉ ባይን የማያዩት
ስም የሌለው ነገር በእጅ የማይነኩት ።

በጣም የረቀቀ ባለብዙ መልክ
ዓይነቱ ተነግሮ የማይተረክ ።

መንገዱን ሰውሮ የሚያንከራትት
ትርጓሜ የሌለው ነገር ሆነበት ።

አንዱን መንገድ ትቶ ለመፈለግ ሌላ
ወደ ውሥጡ ዘልቆ ሲሔድ እያሰላ
በጣም ጠልቆ ኖሮ ጮኸና በኋላ ።

የሆነውን እንኳ ሲያቃስት ደንግጦ
ሮጠ መጣና ፈርቶ ተንቀጥቅጦ
አይለምደኝም አለኝ ክፉኛ ተናውጦ ።



እሱስ ለካ ዘልቆ የሐሳብን ሥሩ
ፈልጎ ለማግኘት ኋኍቶ ሲንጠራራ
ተገናኝቶ ኖሩዋል ከማያልቀው ጋራ ።

## ዓ ለ ም ና  ጊ ዜ ።

እኔማ አቶ ጊዜ ከጥንትም ጀምሬ
ለዓለም ታዛቢ ሆኜ በመኖሬ ።

እጅግ በረዘመው በራቀው መንገዴ
ቸኩዬ በፍጥነት ሳልፍ እንደልማዴ ።

ከቶ አይቀርምና ዓይቶ መመልከት
ትልቅ ግቢ ዓይቼ ባለብዙ ቤት ።

ከደጅ ሲተራመስ ሰዉ ከቤት ተርፎ
ይመስል ነበረ ንብ ያለበት ቀፎ ።

ያጥሮቹ አሠራር የግቢውም መድመቅ
የቤቶቹ አበዛዝ በጣም የሚደንቅ ።

እንደዚህ ግቢውን ሠርቶ እያሳመረ
ማን ይሆን አልኩና ከዚህ የሰፈረ ።

ደንቆኝ ስመለከት በጣም ተገርሜ
ሰው አገኘሁና አልኩት በል ወንድሜ ።

www.ethiopianorthodox.org

የዚህ የውብ ግቢ ባለቤቱ ማነው
ያባት ያያቱ ርስት ያንድ ከበርቴ ነው ።
ርስቱም ዘለዓለም አለ ሳይነካ
ብሎ መለሰልኝ ከርቶ እየተመካ ።

ብዙ ትውልድ አልፎ ለትውልድ ደርሼ
ደግሞ በዚያው መንገድ መጣሁ ተመልሼ ።

ከዚያ ከጥር ግቢ ከዚያ ሁሉ ቤት
ከቁመቱ መርዘም ከጐኑ ስፋት
አንድ ድንጋይ እንኳን ጠፍቶ ምልክት ።
ያ ያየሁት ሁሉ እንዳልነበር ሆኖ
ከግቢው ቦታ ላይ ዓየሁ ትልቅ መስኖ ።
የለመለመበት አንድ ትልቅ ጨፌ
እየተመለከትኩ ልሔድ ስል አልፌ ።
ካንድ ትልቅ ዛፍ ስር ተጠግቶ ጥላ
አንድ እረኛ አገኘሁ ከብቶች ሣር ሲያበላ ።
እንደዚህ ያለ ሣር የበቀለበት
ከመቼ ወዲህ ነው ብዬ ጠየቅሁት ።
እሱም ቁጭ እንዳለ ቀና ብሎ አይቶኝ
ዘለዓለም ለከብቶች ግጦሽ የሚገኝ
ከዚህ ከመስኖ ነው ሲል መለሰልኝ ።

ብዙ ትውልድ አልፎ ለትውልድ ደርሼ
ደግሞ በዚያው መንገድ መጣሁ ተመልሼ ።



መስኖውም ጠፍቶና ጨፌነቱ ቀርቶ
ከመስኩ ቦታ ላይ ከተማ ተሠርቶ ።
የቤቱ መበርከት የመንገዱ ማማር
የከተማው ጥዳት የግንቡም አሠራር ።
የሕዝቡ አበዛዝ የገበያው መድመቅ
ታይቶ እማይጠገብ እጅግ የሚደነቅ ።
ያማረች ከተማ የጥበብ መዝገብ
ጠንቶ የቆመበት አዋጅና ደምብ ።
ውበቷን አድንቄ ስመለከታት
ዕድሜው የጠና ሰው አግኝቼ ድንገት
መቼ ነው የተሠራች ብዬ ጠየቅሁት ።
እሱም መለሰልኝ በጣቱ አመልክቶ
ይቺ ትልቅ ከተማ ከጥንትም አንሥቶ
መልኳ እየታደሰ ውበቷ እያበራ
ይኖራል ዘለዓለም ሥልጣኗ እንደኮራ ።

ብዙ ትውልድ አልፎ ለትውልድ ደርሼ
ደግሞ በዚያው መንገድ መጣሁ ተመልሼ ።

ከዚያች ከከተማ ጠፍቶ ምልክት
ዓየሁ ከዚያ ቦታ ጫካ በቅሎበት ።
ሲተራመሱበት ጅብ ነበር አንበሳ
በያይነቱም አውሬ አዕዋፍ እንስሳ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉም በየቋንቋው ድምጡን እያሰማ
ለጫካው ሲሰጡት የሚያስፈራ ግርማ ።

የዛፉም አበዛዝ ያውሬው መበርከት
እጅግ አስደናቂ ሆኖ አገኘሁት ።

ደኑን ተመልክቼ ስሔድ እያየሁ
ያገር ሰው የሆነ ድንገት አገኘሁ ።

ዛፍ እንጨቱ በቅሎ ጫካው የደመቀው
ከመቼ ወዲህ ነው ብዬ ብጠይቀው ።

ትክ ብሎ እያየ ጫካ ጫካውን
እንዲህ መለሰልኝ እሱም ተራውን ።

ይህን መጠየቅህ እንግዳ ነህ ለካ
ጥድ የሚበቅልበት ግራርና ወርካ
ጥንቱንም ደን ነው የዘለዓለም ጫካ
እንዱ ሥፍራ ሲለቅ አንዱ እየተተካ
ሁሉም ርስቴ ነች እያለ ሲመካ ።

እየተታለልን ሳናስበው እኛ
ዓለም ሰፈር ሆና ሕዝቡ መንገደኛ ።

ትውልድ ፈሳሽ ወሀ መሬቷም ጅረት
መሆኑን ዘንግቶ ይህ ሁሉ ፍጥረት ።

ስትመለከቱት በሰልፍ ተጉዞ
ሁሉም በየተራው ያልፋል ተያይዞ ።



## የ ሰ ው ዕ ድ ል ።

ኃይለኛው ባላልጋ የኢትዮጵያ ንጉሥ
የመቅደላው ዳኛ አፄ ቴዎድሮስ ።

ከጥንት ጀምሮ ከድኅነታቸው
እጅግ ብዙ ጊዜ ያገለገላቸው
በጣም የሚወዱት ሎሌ ነበራቸው ።

እሱም በጣም አዝኖ እየተመረረ
እንዲህ ሲል አንድ ቀን ቀርቦ ተናገረ ።

እግዜር ያሳይዎት ግርማዊ ጃንሆይ
ችግሬን ላመልክት ጉዳቴን ላሳይ ።

እኔ አሽከርዎ የጥንቱ የጧቱ
ይኸው ብዙ ዘመን ስለፋ በከንቱ ።

ስንቱ ኋላ መጥቶ ማዕረግ ሲያገኝ
ምነው እኔ ብቻ ቀን አይሞላልኝ ።

እንኳንስ ለንጉሥ ላንዳንዱ ሻለቃ
ስንት ሰው ነው አድሮ ለማዕረግ የበቃ ።

በታማኝነቴ እንደዚህ ጠንቼ
ግርማዊነትዎን ስኖር ተጠግቼ
እንዴት እኔ ብቻ ልቅር ተረስቼ ።

ፍርድ አስተካካዩ የብዩኑ ጌታ
እያዘኑ ሰምተው ይህን አቤቱታ ።

www.ethiopianorthodox.org

በምሥጢር ጠሩና አንድ የልፍኝ አሽከር
ባንዱ ብር ሞልቶ ባንደኛው አፈር ።
በመልኩ በጐኑ የሚመሳሰል
እንዲያመጣ አዘዙት ሁለት አገልግል ።
ከዚህም በኋላ ሎሌያቸውን ጠርተው
ሁለቱን አገልግል እፊታቸው አርገው
መርጠህ ከሁለቱ እንደምትፈልገው ።
አንደኛውን ውሰድ ብለው አዘዙት
ሎሌው አስተያይቶ ባይኑ መዝኖት ።
መርጦ ወሰደና አንዱን አገልግል
ከውሥጡ ያለውን ፈትቶ ቢያስተውል ።
አፈሩን ስላየ በጣም ተሳቀቀ
ምቀኛውም ዕጣው መሆኑን አወቀ ።
ንጉሡም መልሰው እንደዚህ አሉት
ጥንቱን ሲፈጠሩ ፊት ካልታደሉት ።
ክብርና ማዕረግን ሰው ቢያስብ ቢመኝ
እልም ነው ተረት ነው መቼም አይገኝ ።
ያርባ ቀን እድልህ ሆኗልና ግራ
ልሥራልህ ብል እንኳን የቸርነት ሥራ ።
ከተሰጠህ ዕጣ አያልፍም ሚዛኑ
ስለዚህ ይቅርብህ በኔ ላይ ማዘኑ ።



አፄ ቴዎድሮስ ደህና መርምረዋል
ስለሰው ልጅ ዕጣ መልካም ተናግረዋል ።
ረጅሙን ማሳጠር አጭሩን ማሳደግ
ጥቁሩን ሰው ማቅላት ቀዩን ጥቁር ማድረግ ።
ብልሆች ጠቢባን አልተቻላቸውም
ዕድልም እንዲህ ነው መድኃኒት የለውም ።
የሰው ልጅ ሞኝ ነው አሥሩን ይመኛል
ዕጣው ያልሰጠውን እንደምን ያገኛል ።

## የ ሰ ው  ጠ ባ ይ ።

አንድ ቀን እግዚአብሔር አራዊትን ሁሉ
ተሰብሰቡ ብሎ አዘዘ በቃሉ
በእስትንፋስ ተፈጥሮ ቆሞ እሚንቀሳቀስ
ካንበሳ ጀምሮ እስከ ትንኝ ድረስ ።
ከሩቅ በታ ሳይቀር ሁሉም እየሮጡ
ቃሉን ለመፈጸም ተሰብስበው መጡ ።
ሁሉም ቀረቡና አንድ እንኳን ሳይቀር
ተከማችተው ሳሉ ከዙፋኑ ስር ።
አስቀድመህ አንተ እስኪ ወደዚህ ና
ብሎ እግዚአብሔር በፊት ዝንጀሮን ጠራና ።

www.ethiopianorthodox.org

እነዚህን ሁሉ ዓይተህ ንገረኝ
መልካቸው ከመልክህ በልጦብህ ቢገኝ ፡፡

ንገረኝ ሳትፈራ ገልጠህ የልብህን
አድሳለሁ አለው የጐደለብህን
ዝንጀሮ መለሰ አቤቱ ጌታዬ
ፊትና ደረቴ እጅና ጭራዬ
ውብ ሆኖ ተሠርቷል ምን ጐደለ ብዬ ፡፡

ምኔ አስቀየመና ምኑን ልለምን
እንደቀሩት ሁሉ እግር የለኝምን ፡፡

ይልቅ አቶ ጅብን ብታድሰው ምነው
አፉ በጣም ሰፊ እግሩም አንካሳ ነው
ቀርበ ቢጠይቁት ጅብም ተጠሩና
ምን ጐደለኝ አለ መልኬ ሁሉ ደህና ፡፡

ይልቅ እንደገና ዘሆን ተመልሶ
እጅግ መልካም ነበር ቢፈጠር ታድሶ ፡፡
ይገባል እግዚአብሔር ሐሳቤን ቢቀበል
ከጆሮው አንስቶ ጭራው ላይ መቀጠል ፡፡
ዘሆንም ሲጠራ ሁሉም እየሳቁ
አድሰኝ ይለዋል ብለው ሲጠብቁ ፡፡
ዘሆን ግን መለሰ መልኬን ሁሉ ደህና
አድርጐ ለሠራኝ ይገባል ምሥጋና ፡፡



እኔስ እስከ ዛሬ በመልኬ አፈጣጠር
አላየሁበትም የሚያስከፋ ነገር ፡፡
መታደስ የሚያሻት አሣ ነባሪ አለች
መልክና ቅርጥ አጥታ የተደበለበለች
ዘለዓለም መሳቂያ ሆና ከምትቀር
እሷ እውነት ያሻታል መልሶ መፈጠር ፡፡
እሷና ሌሎቹ ሁሉም ቢጠየቁ
አንዱ ባንዱ ሲያሾፍ እየተሳሳቁ
ይህ ነገር ጐደለኝ መልኬ በዚህ ከፋ
አድሰህ ፍጠረኝ ብሎ የሚል ጠፋ
እግዚአብሔርም ዓይቶ በመከከላቸው
ነውሩን የሚናገር እንደሌለባቸው
በሉ ሒዱ ብሎ አሰናበታቸው ፡፡

ይህ በውሬ ምሳሌ የተወራው ተረት
መልካም ማስረጃ ነው ለሰዎች ከንቱነት ፡፡
እንደኔ ዝንጀሮ ሳላስቀረው ውጬ
እስኪ ነውራችንን ልናገር ገልጬ ፡፡
ስንመለከተው ተመልሶ ለኛ
እጅግ ያለመጠን ያስቃል ክፉኛ
ደግ ሰው ጨዋ ሰው የሚሉ አማርኛ ፡፡
ትንሽ ቀላል ኢምንት ደካማ ወራዳ
ከንቱ ፍሬ ቢሶች አመለ ገዳዳ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ክፉ አይደለንም ወይ ሰዎች ስንባል ?
አዎን ነኝ ብሎ ቢል ያንቀው ይመስል
ብቻ እንደበታችን ይግደረደራል
አውቆም እንደ ዲዳ በዝም ይዘጋል ፡፡

ግን ቀጣፊው በዕውር ዕውሩ በሽባ
ሽባውም በበራ በራ በተብታባ ፡፡

ተብታባው በኩሩ ኩሩው በቆማጣ
ቆማጣው በመልቲ መልቲ በገጣጣ ፡፡

ገጣጣውም በቢስ ቢስ በቀናተኛ
አንዱ ባንዱ ሲያሾፍ እርስ በርሳችን እኛ ፡፡

ለመሳቁ ጊዜ ደስ ደስ ይለናል
የተዘጋውም አፍ ይከፈትልናል ፡፡

ተግሣጽ የማይቀጣው ሰው የሚሉ ጉድ
ምን ጊዜም አይተወው ይህንን ልማድ ፡፡

ብዙ ትውልድ አልፎ ይምጣ አዲስ ዘመን
ሰዎች አንቀጣም ዘለዓለም ያው ነን ፡፡

እንዳይመሳሰል በመልክ ሰው ሁሉ
የተሠራበትም ልዩ ነው አመሉ ፡፡

መልክና አመሉንም አስተውለን ብናይ
አሌ የማንለው ሐቅ አይዶለም ወይ
ፍጹም ሰው ላይገኝ በዚች ዓለም ላይ ፡፡



ይኸ ሁሉ ፍጥረት ምድርን ያለበሰው
ደግም ይባል ጨዋ ጥሩም ይሁን ሊቅ ሰው ፡፡
በጠቅላላው ሆኖ አንደኛውም ሳይቀር
ሰው ሁሉ ጉደሎ ተደርጎ ሲፈጠር
አንዱ ባንዱ መሳቅ መች ይገባ ነበር ፡፡

## የ ግ ፈ ኞ ች ፍ ር ድ ፡፡

ባራዊት መካከል በሽታ ተነሥቶ
ሁሉም ሲጨነቁ ሕመምተኛው በዝቶ ፡፡

ሳይበሉ ሳይጠጡ ብዙ ቀን ሆኗቸው
ሲወድቁ ሲነሡ ሕመም ተጭኗቸው ፡፡

ከሁሉም ኃይለኛው አንበሳ እንዲህ ሲል
ጮኸ ተናገረ ቆሞ መካከል ፡፡

ታሪኩ እንደሚለን ጥንትም የግዜር ቁጣ
ተልኮ ለቅጣት ባለም ላይ ሲመጣ ፡፡

ዕጣ በመጣጣል ወይም በኑዛዜ
ዓመጽ የሠራው ሰው በተገኘ ጊዜ ፡፡
ፍርዱን ተቀብሎ ባመጹ ሲቀጣ
ከለም ላይ ይጠፋል የወረደው ቁጣ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ አሁንም በኛ ላይ መቅሠፍት
እግዚር አላመጣም ያላንዳች ብልሐት ።

ከመካከላችን ክፉ ዓመጽ የሠራ
አይጠፋም እንፈልግ እናድርግ ምርመራ ።

ክፉ ሥራችንን አንድ እንኳን ሳይቀር
ከራሴ ጀምሬ ሁሉን ልናገር ።

ሁል ጊዜ ሲርበኝ የምበላው ሳጣ
በጉን ከነረኛው ጠብቄ ሲመጣ
ሥጋውን በልቼ ደሙን የምጠጣ ።

እንዲያ ሲጨነቁ የጨከንኩባቸው
አይቀርም ይደርሳል ከእግዜር ፊት ደማቸው ።

ይኸ ሁሉ ግፍ ነው መቅሠፍት የሚያመጣ
ምንም ቅር አይለኝ በፍርድ ብቀጣ ።

ግን እናንተም ደግሞ ሳትዋሹ ሳትፈሩ
ያጠፋችሁትን እስኪ ተናገሩ ።

ቀበሮ መለሰች እንደዚህ ስትል
እርስዎ የሠሩትን ተመልካች ሲያስተውል ።

በጉን ከነረኛው ተርበው ቢበሉ
ኃጢአቱስ የት አለ ምንድነው በደሉ ።

ይልቅስ ተርበው እርስዎ ሲበሏቸው
ለበጉም ለረኛው ትልቅ ነው ክብራቸው ።



ዘሆንና ነብር ጅብና አውራሪስ
ቀጥለው በተራ ያጠፉትን ነፍስ ።

ያፈሰሱትን ደም አንድም ሳይደብቁ
ይህን አጥፍተናል ብለው አስታወቁ ።

ግን ከደባበዩ የነበሩት ሁሉ
ፈርተው በትክክል መፍረድ ስላልቻሉ
ጥፋታችሁ በጣም ቀላል ነው እያሉ ።

እንኳንስ ሊቀጡ ምንም ሳይወቅሷቸው
የሚያስቀጣ አይደለም ብለው ዝም አሏቸው ።

ከሁሉም በኋላ አህያ መጣች
እሷም ተናዘዘች እንዲህ እያለች ።

አንድ ቀን ተጭኜ ደክሞኝ ስንገላታ
ጌታዬ ሲነዳኝ በዱላ እየመታ
ግጦሽ ሣር ዳይቼ ቢርበኝ ጉረስኩ
ያውም አንድ አፍ እንጂ ሌላም አልደገምኩ ።

ሣሩ የሌላ ሰው መሆኑን አውቃለሁ
ግን ሰይጣን ገፋፍቶኝ መስረቄ አጥፍቻለሁ ።

ይህነን ሲሰሙ ሁሉም አንድነት
የስድብ የርግማን የቁጣ መዓት
እያከታተሉ አወረዱባት ።

www.ethiopianorthodox.org

ቀበሮም ተነሥታ ያላንዳች ምሕረት
አንቺ አመዳም እርጉም እከካም ፍጥረት ።

ለካ ባንቺ ጦስ ነው ይህንን በሽታ
በሁላችንም ላይ ያመጣብን ጌታ ።

እንዴት ብትጠግቢ የሰው ሣር በላሽ
ሞት ነው ሌላም አይዶል ላንቺ ቅጣትሽ ።

ብላ በሁሉም ስም ስትጨርስ ተናግራ
ፍርዱም በዚህ ቆመ አለቀ ምርመራ ።
ከዚያ የነበሩት የምድር አራዊት
አዎን አዎን ብለው ይገባታል ሞት
ምስኪኗን አህያ ተከፋፈሏት ።

እውን የቧ ዓመጽ ነው የፈጣሪን ቁጣ ።
ባራዊት ሁሉ ላይ ጐትቶ ያመጣ ።
ከተናዘዙትስ ካራዊቶች ውሥጥ
የቧ ዓመጽ ኖሯል ወይ በእውነት የሚበልጥ ።
ያም ሆነ ያም ሆነ መቸም አልዳነች
ስለሁሉም ኃጢአት አህያ ሞተች ።

እነሆ ባለም ላይ በዳኝነት ሥራ
ጉባዔ ተደርጎ ሲፈጸም ምርመራ ።
ይህን የመሰለ ብይን ይሠራል
ደሃም በመካከል ጠፍቶ ያቀራል ።



## አባት ፤ ልጅ ፤ አህያ ።

አንድ የባላገር ሰው ገንዘብ ቸግሮት
አህያውን ሊሸጥ ተነሥቶ በጧት ።
አህያውም ሲሔድ እገበያ ድረስ
ደክሞት እንዳይከሳ ዋጋ እንዳይቀንስ ።
አራት እግሩን አሥሮ በደህና ቀላድ
ወንድ ልጁን ጠርቶ አለው እንሂድ ።
ልጅና አባት ሆነው አህያን ሁለቱ
ተሸክመው ሔዱ እየተጫወቱ ።
ገና መጀመሪያ አንድ ሰው ሲያያቸው
ስለተገረመ በዚህ በሥራቸው ።
ደንቆት እንደዚህ ሲል ጮኾ ተናገረ
ሳይሠራ እስከሁን ባለም ላይ የቀረ
ከሌላው ጉድ ሁሉ ይህ ብቻ ነበረ ።
ዛሬስ ብሎ ብሎ ሥራ ቢያጣ ደግሞ
አህያን በጫንቃው ሰዉ ተሸክሞ ።
ይንቀረፈፍ ጀመር ይኸው ባገራችን
እንዲህ ያለ ታሪክ አልሰማም ጆሮዋችን ።
ይልቅስ ሌላ ሰው አይይ ይኸን ጉድ
አህያውም ይውረድ በእግሩ ይራመድ ።
እያለ በማሾፍ ስለሳቀባቸው
የተገባ ምክር ስለመሰላቸው
አባትና ልጁ አህያውን ፈትተው

www.ethiopianorthodox.org

ይነዱት ጀመረ እንደ ደንበ ገብተው
ከትከሻ አውርደው እንንዳህ ቢሉት
ከዕረፍት ወደ ድካም ስለሆነበት ።

አህያው ለግም መቆም ስላመጣ
ልጅየው ተናዶ ከህያው ላይ ወጣ ።

ከዚያም እየመታው በደህና ጐመድ
ይጓዙ ጀመረ በባቡር መንገድ
አንድ ሽማግሌ ራስ መላጣ
ይህን ነገር ዓይቶ እንዲህ ሲል ተቆጣ
መቸም የዛሬ ልጅ ለምንም አይረባ
በፍጹም ጠያፍ ነው ጭራሽ ያልተገባ ።

አባት በእግሩ ሲሔድ ልጅየው በከብት
ምነው እንዲህ ነወይ ሲከበር አባት ።

ብሎ በልጁ ላይ ተግሣጽ ቢናገር
መልስም አልመለሰ ሳይከራከር ።

ደንግጦ ልጅየው ወረደና ቶሎ
አባት ተቀምጦ ልጁ ተከትሎ ።

ጥቂት እልፍ ብለው ቁልቁለት ሲወርዱ
ሶስት ሴቶች ሆነው አንድነት ሲሔዱ ።

አንዷ ተናገረች እንደዚህ ስትል
ልጁን አስከትሎ አሽከር ይመስል ።



ደልቶት ከህያ ላይ ይህ የተቀመጠው
ሲሆን ቢወርድለት ወይ ቢያፈናጥጠው ።

ቢለወጥ ነው እንጂ ጊዜና ዘመኑ
አባት በልጁ ላይ እንዲህ መጨከኑ ።

አባትየው ሰምቶ ይህንን ስትል
ነውር መስሎ ታየው ልጁን ማስከተል ።

ደስ ይበላት ብሎ ጠርቶ አፈናጠጠው
አባትና ልጁ አንድነት ተቀምጠው ።

ጥቂት እንደሔዱ አንዱ ደግሞ ዓይቷቸው
እሱም እየሳቀ እንደዚህ አላቸው ።

አሁን ይህ አህያ እገበያ ድረስ
እውነት ይችላል ወይ ሳይሞት ለመድረስ ።

እንደዚህ ሆናችሁ ገበያ የምትወጡ
ምናልባት ይሆናል ቆዳውን ልትሸጡ ።

አሁንም ይሻላል ብትወርዱለት
አህያችሁ ደክሞ መንገድ እንዳይሞት ።

ሰምተው እንዳልሰማ አልፈው እንዳይሔዱ
አባትና ልጁ ሁለቱም ወረዱ ።

አህያው ሌጣውን እነሱም በእግራቸው
ይጓዙ ጀመረ ወደ ገበያቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ አልበቃ ብሎ ጥቂት እልፍ ሲሉ
ሰዎች ሳቁባቸው እንደዚሁ እያሉ ።

ሌጣ አህያ ነድተው ፊት እያስቀደሙ
የማናቸው ጅሎች በእግር የሚደክሙ ።

ሌጣ አህያ ነድቶ በእግር መኳተን
ትልቅ ኩብትንት ነው አህያ መሆን ።

አባት ይህን ጊዜ መለሰ እንዲህ ሲል
በጣሙን ሲያንሰኝ ነው አህያ መባል ።

ባለማወቃችን በጣም ተታለን
ሁሉን ደስ ማሰኘት የሚቻል መስሎን ።

ሰው በሳቀ ቊጥር እውነት መስሎን ጉድ
ይህ ሁሉ ጕዳና ይህ ሁሉ መንገድ ።

ዘለቅነው እስከዚህ ስንወጣ ስንወርድ ።
ከእንግዲህ ወዲያ ግን ይጥላም ይቀበል ።

በቃኝ የሰው ነገር ሰምቶ መከተል
እነሆ እንደዚህ ነው የዚህ ዓለም ጣጣ
ማናቸውም ነገር ተቃንቶ ቢዋጣ
ሰዉ በሰው ነገር የሚለው ላያጣ ።

የሁሉን ቃል ሰምቶ እንዴት ይዘለቃል
ሰው ለራሱ ጥቅም ያሰበው ይበቃል ።



ደግነትና ክፋት ።

አንድ ሰው ነበረ ቅንነትን ወዳድ
ለሁሉ ማዘንን አድርጎ እንደልማድ ።
ይኖር የነበረ ነቅቶ እንደ ዘበኛ
ደግ ሥራ ለመሥራት ልቡናው ሳይተኛ ።
አንድ ቀን ማለዳ ተነሥቶ ሲሔድ
እባብ ወድቆ አገኘ ከማህል መንገድ ።
አመዳይ ጥሎበት ውርጭ አቆራምዶት
አሥራ አምስት ደቂቃ የቀረው ሊሞት
ሰውየውም አዝኖ ይህን በማየት
ከመሬት አንሥቶ በጁ ጨብጦት ።
ከቤቱ አገባና በድኑን እባብ
ዘርግቶ አስቀመጠው ምድጃ አጠገብ ።
እሳት እያሞቀ ጥቂት እንዳቆየው
እጥፍ ዘርጋ እያለ ሲንቀሳቀስ ዓየው
ሰውነቱ ሞቆ ሕይወት ሲሰማው
ተንከልና ቁጣ አንድነት ሆነው ።
የተፈጥሮው ክፋት በሐሳቡ መጥቶ
የሚነክሰው ሲሻ መላሱን አውጥቶ ።
ሞቶ የነበረው ያ በድን እሬሳ
ያዳነውን ሊነድፍ ራሱን አነሣ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሰውየውም ዓይቶ ይህን አኳኋን
በሠራው ደግነት አዘነ በውን
ምንም ክፋት ለሱ ገንዘቡ ባይሆን ።
ደጉን ክፉ አድራጊ የተገባ ቁጣ
እንደ እሳት ተፋጅቶ በልቡ ላይ መጣ ።
መጥረቢያ አነሣና እባቡን ቢለው
ከራት ላይ ቆርጦ በጣጥሶ ጣለው ።
ሰው ደግ ሲውልለት እባብ እየከዳ
በደግ አድራጊው ላይ መርዙን አሰናዳ ።
ክፉም ሰው እንደዚሁ የክፋቱ ክፋት
ደግ የዋለለትን ያስባል ለማጥፋት ።
ተንኮሉም በሰበው መንገድ መሔድ ትቶ
የገዛ ጥፋቱን ያመጣል ጐትቶ ።

## ምሥጢርና ወሬ ።

ምሥጢር አጫውተዋት ምን ቢኋት አደራ
ጠብቃ የምትኖር ለሰው ሳታወራ ።
ባለም ላይ ምንም ሴት አትገኝም ከቶ
ብለው በጨዋታ ሲናገሩ ሰምቶ ።
አስቦ ሊረዳ እውነትነቱን
አንዱ ሰው ፈለገ ሚስቱን ሊፈትን ።



ማታ መብራት ጠፍቶ ሁለቱም ተኝተው
ምነው ሆዴን ወጋኝ እንጀቴን ጐተተው ።
የነከኝን እንጃ አባክሽ ተነሺ
እስኪ መብራት አብሪ ልብስሽን ልበሺ ።
አለና ባልየው ሚስቱን አስነሣት
እሷም ቶሎ ለብሳ ስታነድ እሳት ።
አንቺ ልጅ ጉድ በዩ ዛሬ እኔ ጉድ ሆንኩ
ልክ የዶሮ መሰይ እንቁላል ወለድኩ ።
አለና እውነትም የዶሮ እሚመስል
ሰጣት ለሚስቲቱ ትኩስ እንቁላል ።
እሷም በጣም ገርሟት እያገላበጠች
ካየችው በኋላ ወስዳ አስቀመጠች ።
ባልየው ለሚስቱ እንደዚሁ አላት
ይህ ነገር እንግዲህ እንዲያው ምናልባት ።
ሰው ቢሰማውና አገር ቢያወራው
ለኔም ሆነ ላንቺ ትልቅ ነውር ነው ።
ለሰሚው መሳቂያ መሆኔን እወቂ
ለማንም አታውሪ በጣም ተጠንቀቂ
ሚስቲቱ መለሰች ምኑን ያወሩታል
መልከም ወሬ ቢሆን እርግጥ ያዋዩታል ።
ይኸ ለራሱ ጉድ ታይቶ ያልታወቀ
እንዲያው ይቅር እንጂ እንደተደበቀ ።

www.ethiopianorthodox.org

## በዓመጽ የመጣ ገንዘብ ።

አንድ ሀብታም ነጋዴ ሲጓዝ አግኝተው
ሦስት ሌቦች ሆነው ወርቁን ቀምተው ።
እሱንም አርደውት ከጉድባ ጣሉት
ሁለቱ አንደኛውን እንደዚህ አሉት ።
ገንዘብም አገኘን እንግዲህ ሔደህ
ከከተማ ምግብ ብዙ ገዝተህ ።
ሳትውል ሳታድር ይዘህ ቶሎና
ጠም ውለን ጠም ካደርን ብዙ ቀን ነውና ።
እሱም እሺ ብሎ ተነሥቶ ሲሔድ
እንዲህ ሲል አሰበ መንገድ ለመንገድ ።
አብረውኝ ባይኖሩ እኒህ ጓደኞቼ
ወርቁን ለኔ ብቻ ወስጄ አስቀርቼ ።
እከብር ነበረ አሁን ግን ለሦስት
ስንከፍለው ይሆናል ድርሻችን ጥቂት ።
አስቦ ለብቻው ወርቁን ለመውሰድ
ዘዴ በመፈለግ ሲያወጣ ሲያወርድ ።
መርዝ ፈለገና ከሚበሉት ውሥጥ
ጨምሮ ወሰደ ለነዚያ ሊሰጥ ።
እነዚያም ባንድ ወገን እንደዚህ አሰቡ
ወርቁስ ብንሸጠው ብዙ ነው ሂሳቡ ።



ብቻ ምን ይሆናል ያ የኛ ጓደኛ
ተካፋይ የሆነ አለብን ሦስተኛ ።

ግን ለሁላታችን ብቻ ብናስቀረው
የሚያንሰን አይዶለም ድርሻችን በቂ ነው ።

ተማክረው ሲመጣ በጩቤ አርደውት
እሱንም ከጉድባ ገድለው ጨመሩት ።

ተርበዋልና ቶሎ እንደቸከሉ
ምግቡን አሰናድተው ምሳቸውን በሉ ።

ጥቂት እንደቆዩ ሕመም ተሰማቸው
መርዙም ተሰራጭቶ በሰውነታቸው
ወዲያው ሁለቱንም እዚያው ገደላቸው ።

ከነከረጢቱ ወርቁ እንደታሰረ
ባለቤት የሌለው ገንዘብ ሆኖ ቀረ ።

በመሥራት ነው እንጂ ላብን በመጥረግ
በመስረቅ በመንጠቅ የለም መበልጠግ ።

ቀጥራቸው ብዙ ነው ግፍ ሠርተው በከንቱ
ባመጽ የሰው ገንዘብ ሰብስበው ሲከቱ
ደም እያነቃቸው ሳይበሉት የሞቱ ።

www.ethiopianorthodox.org

## የሀብት ትዕቢት ።

ብዙ ብርና እህል በጭነት የያዙ
ሁለት አጋሰሶች አንድነት ሲጓዙ ።
ብሩን የተጫነው ጓደኛውን አለው
እንዴት አንተን ከኔ እኩል አስተካከለው ።
አብረን እየነዱን እኩል እንሒድ
እኔ ተከብሬ በጣም ብወደድ ።
አደራ ሰጥተውኝ ብር ጭነውኛል
ካንተ ግን ያነሰ ምን ፍጡር ይገኛል ።
እነሱም አውቀውት መሆንህን ታናሽ
አድርገውህ ቀሩ እህል አመላላሽ ።
መራመድህ ቀርቶ እኩል ከኔ ጋራ
መሥራት ይገባሃል የሥልጣኔ ሥራ ።
ይልቅ ያልተቀጣ ባለጌ አትምሰል
ወደ ኋላ ቀርተህ እኔን ተከተል ።
እያለ በንቀት ሲናገር ትዕቢት
ሁለት ሌቦች ወጥተው ካደፈጡበት ።
እህሉን ተዉና ብሩን ሲፈልጉ
በዱላ ደብድበው በጩቤ እየወጉ ።
ብር የተጫነውን አጋሰስ ገድለው
ወሰዱት ይባላል ብሩን ተካፍለው ።



አስተውለህ አንባቢ መሆኑን ትምህርት
የዚህን የተረት ምሥጢር ተመልከት ።
ከብሬያለሁ ብሎ ሰውም እንዳይኮራ
በገንዘብም እንዲህ አለበት መከራ ።

## የከፋት ተጋብዖነት ።

አንድ ከሰል ሻጭ ልብስ አጣቢን አለው
ለቤት ኪራይ ብለህ ገንዘብ የምትከፍለው ።
ቀሪ እንዲሆንልህ አብረህ ከኔ ጋራ
ኪራይ ሳትከፍል ተቀምጠህ ብትሠራ ።
ቤቱም ይበቃናል አብረን እንኑር
ልብስ አጣቢው ሰምቶ ይህንን ምክር ።
ለኔ በማሰብህ እግዜር ይስጥልኝ
ግን የማይጠቅመኝ ነው የማይስማማኝ ።
ታጥበ ታጥበ ጭቃ የሚባለው ተረት
እንደሚደርስብኝ አስበህ ተመልከት ።
እኔ የማጥበው ልብስ ካንተ ከሰል ጋራ
ይቆሽሽ የለም ወይ አብረን ስንሠራ ።
ከሰል ለንጭ ልብስ ነውና ጠላት
የማይሆን ሐሳብ ነው ሲል መለሰለት ።

www.ethiopianorthodox.org

ከሰል ለነጭ ልብስ እንዲሆነው አጥፌ
ከከፋም የዋለ ክፋትን አትራፊ ።
ከመሆን አይድንም ምን ቢጠነቀቅ
አመል ሳይበላሽ ጠርቶ እንዲጠበቅ
ከመጥፎ ጓደኛ ይገባል መራቅ ።

---

## ሁ ለ ት  ወ ን ድ ማ ማ ቾ ች ።

ያንድ እናት ያንድ አባት ሁለት ልጆች
ታላቅና ታናሽ ወንድማማቾች ።
አባታቸው ሞቶ ቅርሱን ሲካፈሉ
ሁለቱ አንድ አህያ ደረሳቸው አሉ ።
ታናሽ ደሀ ነበር ታላቁ ግን ጌታ
እንዳይቀርባቸው የሁለቱም ፈንታ ።
ታናሹ እንሽጥ ቢል ታላቁ እንረድ
በዚህ ተጣሉና ሔዱ ወደ ፍርድ ።
የሁለቱን ሐሳብ ዳኛ ተመልክቶ
የታላቁን ተንኰል መርምሮ ተረድቶ
መሸነት ቢያቅተው ሁለቱን አስማምቶ ።
ታላቁ እምቢ ብሎ እንረደው ካለ
የሚከለክለው ምንም ነገር የለ ።



አለና ባጭሩ ብይኑን ሰጣቸው
አህያውም ታርዶ ተከፍሎ ድርሻቸው ።
ሀብታሙ ድርሻውን ሰጠ ለውሾቹ
ከዚያ ቀን ጀምሮ ወንድማማቾቹ ።
በጠብ ተለያይተው ተቀያይመው ቀሩ
ካባታቸው ርስት ተካፍለው ሲኖሩ ።
ሀብታሙ ታላላቅ አደራሾች ሠርቶ
ታናሹም ለብቻው ካንድ ጐጆ ገብቶ ።
ቂም ይዞ በሆዱ ወንድሙን ሊጐዳ
ብድሩን ሊመልስ አንድ ቀን ማለዳ ።
ከቤቱ ተነሥቶ ዛሬ ይኸውና
ጐጆዬን ማቃጠል ፈልጌያለሁና ።
ከዳራሾችህ ላይ እሳቱ እንዳይደርስ
ቶሎ ዘዴ ፈልግ ኋላ እንዳታለቅስ ።
አለና ነገረው ለታላቅ ወንድሙ
የወንድሙ ቤቶች ይህንን ሲሰሙ ።
ሁሉም ተሸበሩ ወንድሙም ተናዶ
ባንተ ጐጆ ሰበብ ቤቴ ለምን ነዶ ።
የጐጆህን ዋጋ ሂሳቡን ሰጥቼ
አስቀራለሁ እንጂ በገንዘብ ገዝቼ ።
ቢለው ታናሽየው ምነው ምን ቢያቀብጥ
ዓይኔ እያየ ላንተ ቤቴን የምሸጥ ።

www.ethiopianorthodox.org

ማን ይከለክላል ባደርግ እንዳሳቤ
አቃጥለዋለሁ በገዛ ገንዘቤ ።
በዚህ ተጣሉና ወደ ዳኛ ወጥተው
ዳኛውም ዓየና ማስታረቅ ቢያቅተው ።
ወዶ ከተነሣ ቤቱን ለማቃጠል
እንዴት ይቻለናል እኛ ለመከልከል ።
ብሎ ለታናሹ ስለበየነለት
እሳት ከጐጆው ላይ ወስዶ ለኮሰበት ።
እሳቱንም ነፋስ እያስተላለፈው
ከዚያ ሁሉ አዳራሽ አንድ እንኳን ሳይተርፈው ።
ባዶ ሜዳ ቀረ ሁሉን አቃጥሎት
በኋላም ታናሹ ድርሻውን መሬት
ሁዳድ አረሰና አተር ዘራበት
የወንድሙ ልጆች አተሩ ሲሸት ።
እንቡጡን ፈልፍለው ሲበሉ ያዛቸው
የበሉትን አተር አሁን አምጡ አላቸው
ወንድምየው ደርሶ እከፍላለሁ ቢለው
ለምንድነው እኔ ዋጋ እምከፈለው ።
ቢፈልጉ ቀደው ከሆዳቸው ያውጡ
የበሉትን አተር አሁን ካላመጡ ።
አለቅም አለና ልጆቹን ያዛቸው
ወንድማማቾቹ እንደልማዳቸው ።



ፍርድ ይለየን ብለው ደግሞ በዚህ ነገር
ተጣልተው ለሙግት ሔዱ ወደ ወንበር ።
ያመጣበት ዳኛ ነገሩን አስተውሎ
ታናሹን ተከሰህ ተገላገል ብሎ ።
ታናሹ እምቢ ብሎ ኃይል ቃል ቢያመጣ
እንግዲህ አተሩን ከሆዳቸው ያውጣ ።
ምን ማድረግ ይቻላል አለና ፈረደ
የወንድሙን ልጆች ሆድ እየቀደደ
ታናሽየው ወንድም አተሩን ወሰደ ።

ሲስማማ ነው እንጂ የሰው ልጅ ኩራቱ
መፋቀር ከሌለ ብዙ ነው ጉዳቱ ።

ታላቅ በጌትነት በገንዘቡ ኮርቶ
ወንድሙን ሊጐዳ በጥጋብ ተነሥቶ
አህያን ባያርደው ታናሽ ተቆጥቶ ።

ብድሩን ሊመልስ ወንድሙን ሊቀጣ
ይህን ሁሉ ጉዳት ኋላ ባላመጣ ።

እብሪትና ክፋት የሚያመጡት ዕዳ
አያልቅም ይባላል ቢቀዳ ቢቀዳ ።

ብትንቁት እንኳን ቂሙን ባትፈሩ
ስዎች በማንም ላይ ክፉ ሥራ አትሥሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ጥ በ ብ ።

ያቺን ትንሽ ፍጥረት ንብን ተመልከቱ
አታሳልፈውም ጊዜዋን በከንቱ ።
ትመላለሳለች ገደል ሳትል ሜዳ
አበባ ልትቀስም ወሀ ልትቀዳ ።
ከደከመችና ከሠራች በኋላ
ተመጋቢ ሁሉ ማሯን እንዲበላ ።
ጉንዳንን አስተውሉት ገበያተኛ መስሎ
ሁሉም ባንድ መንገድ ሲሄድ ተከታትሎ ።
እሱም ይዋትታል ዳገት ሳይል ሜዳ
ለክረምት የሚሆን ስንቁን ሲያሰናዳ ።
ዎፍም ትደክማለች ታያለች መከራ
ልጆቿን ልትቀልብ ጐጆ ልትሠራ ።
ማንኛውም ቢሆን ጥበብ የተባለ
ሳይደክሙ የሚገኝ ምንም ነገር የለ ።
ጊዜው ተላላፊ የማይመለስ
መሆኑን እያወቅን ሳንንቀሳቀስ
እንዴት ሰዎች እኛ ከንስሳ እንነስ ።
ተነሡ እባካችሁ ስለዚህ ድከሙ
ሊቃውንት በመጽሐፍ የሚሉትን ስሙ ።



ትጉ ሥሩ ልፉ ለሥልጣኔ አስቡ
ጥበብን ፈልጉ መጽሐፍን አንብቡ ።
መጽሐፍን አንብቡ ከሁሉም ይልቅ
ቢቀዳ ቢቀዳ ጥቅሙ የማያልቅ ።
መጽሐፍ ፀሐይ ሆኖ ሁሉንም እውቀት
አብርቶ ያሳያል ለሚፈልጉት ።
መጽሐፍ ዓይናችሁ ነው የልብ ሠብራት
ደግና ክፉውን የምትለዩበት ።
መጽሐፍ ቃል ኪዳን ነው ሁሉን የሚያለማ ።
ሰውን የሚያፋቅር ሕዝብን የሚያስማማ ።
በመጽሐፍ ትርጉም ነው በቃሉ ምሥጢር
ነፍሳችን ራሷን የምትመረምር ።
ይገባል ስለዚህ ለማግኘት ጥበብ
በያይነቱ ሰጥቶ መጽሐፉን ለሕዝብ
ትርጉሙን ማጠጣት ቃሉን መመገብ ።

## ሰ ው ና ታ ሪ ክ ።

ንጉሥም አዋቂም ጐበዝም አርበኛ
ሀብታምም ነጋዴም የሕዝበችም ዳኛ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ሕይወት አንቅልፍ ነች ።

ዓለም ዓለም ሲሉሽ ስምሽ ደስ ያሰኛል
ግን ካንቺ የከፋ ምን ነገር ይገኛል ።
ሕግሽ ጠማማ ነው ዘመንሽ ጠቋራ
ክብርሽ ልክስክስ ነው ደስታሽ መራራ ።
ስንቱ ተታለለ አንቺን የሚመኝ
እውነትሽ ሐሰትሽ በውል አይገኝ ።
ቃልሽ ወላዋይ ነው ግዝትሽ ይከዳል
ብይንሽ ዕውር ነው ፍቅርሽም ይጐዳል ።
እኔን የሚገርመኝ አወይ አንቺ ዓለም
ይኸ ሁሉ ሲሆን የሚጠላሽ የለም ።
ያላንዳች ምክንያት ባማሽም አይበጅ
ሥራሽን ገልጬ ልናገረው እንጅ ።
የዳኛ ቀማኛ የሥረኛ ንጹሕ
የመኳንንት ቂል የደሀ ብልህ ።
ያዋቂ ገልጃጃ የሞኝ ብልሐተኛ
ያረመኔ መልከም የቄስ አመጸኛ ።
የችግረኛ ቸር የሀብታም ንፉግ
የወዳጅ ከሐዲ የባላንጣ ደግ ።
መኖሩን አስተውለን በዚህ ዓለም ላይ
ጠልቀን ስናስበው መርምረን ስናይ ።



በጣም የሚያስቸግር ምሥጢር አለበት
ብልህ ሰው ይራባል ደንቆሮው ተርፎት
ሠራተኛም አጥቶ በችግር ሲሞት
ሰነፍ ይጨፍራል ገንዘብ አስክሮት ።
መጻፍን አንብቦ ይህን ሲያስተውል
ያልሠራ እንዳይበላ የሚለውን ቃል
እያየ ከመሳቅ ማነው ዝም የሚል ።
አንዳንዱ ሰው ደግሞ ገንዘብ አለኝ ብሎ
በበታቾቹ ላይ ግፍ ሲሠራ ውሎ ።
ደስ ብሎት ይገባል ማታ ወደ ቤቱ
ብዙ ደሀ ደግሞ ገንዘብ በማጣቱ ።
ግፉን ተቀብሎ በደባባይ ፊት
አልቅሶ ይቀራል አጥቶ ዳኝነት ።
ነገሩማ ከጥንት እንደሚነገር
ዳኝነት የቆመው ለደሆች ነበር ።
ከዚህ ሁሉ ደግሞ በጣም የሚብስ
የሰው ልጅ ሲወለድ ገና ሲጸነስ ።
አንዱ ልዑል ሆኖ አንደኛው ባላልጋ
አንዱ ሀብታም ሆኖ አንዱ ባለጠጋ ።
አንዱ ደሀ ሆኖ አንዱ ችግረኛ
አንዱ ዕውር ሆኖ አንዱ በሽተኛ ።
የበላይ የበታች ሆኖ ይወለዳል
አንደኛው ሲጠቀም አንደኛው ይጐዳል ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመወለድ በፊት መበላለጣቸው
በምግባራቸው ነው ወይስ በሥራቸው ።
አንደኛው ሲታደል አንዱ ያልታደለ
ያ ምን መልካም ሠርቶ ይኸስ ምን በደለ።
ደግሞ ስንቱ ዋሽቶ ቀላምዶ ይከብራል
ስንቱ በውነት መንገድ ሥራውን ይሠራል
እውነት በመውደዱም ተንቆ ይኖራል ።
ይህን ሁሉ ካየን ባለም ላይ ሲሠራ
እኛም እንዲህ እንበል ከፈላስፋው ጋራ ።
ይች ዓለም አልጋ ነች ዕድሜ እንቅልፍ ናት
ደስታም እልም ነው ኀዘንም ቅዠት
ከእንቅልፉ ጋር አልፎ ይህ ሁሉ ስሕተት
ተገልጦ ሊታየው የዓለም ከንቱነት
ከእንቅልፉ ይነቃል ሰው የሞተለት ።

## ባ ል ና ሚ ስ ት ።

በተክሊል ተጋብተው ቈርበው የሚኖሩ
አንድ ሊቅ ሰውና አንዲት ሴት ነበሩ ።
ከተጋቡ ወዲያው አንድ ዓመት ሳይሆን
ጠብና ጭቅጭቅ የሌለው መጠን ።
እየተነሣሣ በመካከላቸው
ሁሉ ቀን ጧት ማታ ስላበሳጫቸው ።



ምንም ቢቻቻሉ እንደዚህ ሊዘልቁ
የማይችሉት ነገር መሆኑን አወቁ ።
የቁርባኑም ነገር ስለከበዳቸው
የመፋታት ሐሳብ ግራ ሆነባቸው ።
ሽማግሌ ዘመድ ቄስም በነገሩ
ብልሐት ሲሹለት በብዙ መከሩ ።
ባልና ሚስቲቱም ተክሊል ሳያፈርሱ
በቄስ ተማምለው ተስማምተው ጨረሱ ።
አብረውም ሳይኖሩ ተክሊሉን ለማክበር
የሚችሉበትን ብልሐት ይሹ ጀመር ።
በኋላም ቤታቸው ለየብቻ ሆኖ
አኗኗራቸውም በደንብ ተወስኖ ።
ጋብቻውም ሳይፈርስ ቤቱን ግን ለይተው
እንዳይለያዩ ሁለቱም ተስማምተው ።
በዚህ ሐሳብ ረግተው ይኖሩ ጀመር
ለመጫወትና ለመነጋገር ።
በፈለጉ ጊዜ አይችሉም ሁለቱ
ከኩል ሰዓት በላይ አብረው ሊጫወቱ ።
ጥቂት እንደቆዩ ይመጣል ጠባቸው
ወይ እሱ ወይ እሷ ከሁለት አንዳቸው
ተነሥተው ካልሄዱ አይበርድም ጥላቸው ።
ይልቁንም እሱ ጭቅጭቁን ትቶ
ግና ጠብ ሲነሣ ይሄዳል ተነሥቶ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከትልቅ ኃይልና ከብዙ ጉልበት
ምንም ትንሽ ቢሆን ይበልጣል ብልሐት ፡፡

## እ ው ቀ ት ና  ክ ፋ ት ፡፡

ብዙ ሰዎች አሉ ባህርያቸው የከፋ
አዋቂዎች ተብለው ስማቸው የጠፋ ፡፡
በእውቀት ተመስግነው በጣም የተማሩ
ጥበብና እውቀትን የተመራመሩ ፡፡
ግን በሕይወታቸው ባለም ላይ ሲኖሩ
ብዙ መጥፎ ሥራ በሰው እየሠሩ
ተሰድበው ተጠልተው ተንቀው የቀሩ ፡፡
የነዚህን ሰዎች ምግባር በማየት
መማር መመራመር መጣጣር ለእውቀት ፡፡
ለምንም አይጠቅም ከንቱ ነው እያሉ
ብዙ ሰዎች ደግሞ ስሕተት ያስባሉ ፡፡
ግን በጣም መርምረው ቢመለከቱት
ቶሎ ይረዱታል መሆኑን ስሕተት ፡፡
በመድፍ በሽጉጥ በጦር በጠመንጃ
ለስሕተትነቱም እነሆ ማስረጃ ፡፡
ጠበንጃና ሽጉጥ ሌላም ጦር መሣሪያ
ይጠቀማል በማለት ሠሩት መጀመሪያ ፡፡



ኋላ ግን ተገኘ አባቱ ልጁን
ልጅም ወላጆቹን ሰውም ወዳጁን ፡፡
ሕዝቦችን ባለም ላይ እርስ በራሳቸው
በቁጣና በጠብ ሲያገዳድላቸው ፡፡
ደግሞ ባንድ በኩል ጠላት ለመግፋት
አዋጅ ለማስፈጸም ድንበር ለማስፋት ፡፡
ለመንግሥቶች በጣም ስላገለገለ
ጦር መ ሣሪያ መሥራት ዩቅር መች ተባለ ፡፡
እንደዚሁም ደግሞ ብናመዛዝነው
እውቀትም ለመንፈስ የጦር መሣሪያ ነው ፡፡
እስቦ በልቡ የሚጠቅመውን
ሰው እንደ ወደደ ክፉንም ደጉን
ለመሥራት ይችላል የፈለገውን ፡፡
ሰው ስለተማረ ስላለው እውቀት
ሊታገድ አይችልም ክፉ ከመሥራት ፡፡
ሕሊናው መዝኖ ግብሩን ካልወሰነው
እውቀት ሠራተኛ አዛዥ ጠባይ ነው ፡፡

## አ ይ ጥ ና  ድ መ ት ፡፡

አንድ ትልቅ ድመት አይጦች በልቶ በልቶ
ጠግቦ ከጣራ ላይ እንቅልፍ ተኝቶ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

እንዴት አይጥ መጥታ ልጆቼን በልተህ
አንተ ደስ ብሎሃል ጠግበህ ተኝተህ ።
እኔ ምስኪኒቷ ጉልበት ስላጣሁ
ልጆቼን አጥቼ አልቅሼ ቀረሁ ።
ደግሞ እንደ ደጉቹ አርፈህ የምትተኛ
እንቅልፍ የተሠራው ለጨካኝ ደመኛ
አንተን ለመሰለ ለከፋ ዓመጸኛ ።
መቼ ሆነና ነው ብላ እያለቀሰች
ስትናገር ሰምታ ዘመዷ የሆነች ።
ቀርባ እህቴ ሆይ አንቺም አንዴት አይጥ
ድምጥሽን አጥፍተሽ እንደመቀመጥ ።
የተናገርሽውን አሁን ቢሰማሽ
ትቀሪ ነበረ አንቺም ተበልተሽ ።
እኛም እንዳንጠፋ ሞት እንዳይመጣብን
የተኛውን ድመት መቀስቀስ ይቅርብን ።
እያለች ዘመዷን መክራና አስረድታ
ይዛ ሔደች አሉ በግድ ጉትታ ።

## ሥ ራ ።

እንደ ሐምሌ ሌሊት ጨለማውን ለብሶ ።
በኖረበት ዘመን ድንቁርና ነግሶ ።



ግማሹ ተቀምጦ ግማሹ ሲሠራ
እኩሉ ሲገብር የቀረው ሲከራ ።
በደልና ግፍም ከባድ ሸክም ሆነው
በደሀ ጫንቃ ላይ ሲኖሩ ተጭነው ።
ደሀን በመሰለ በጨለማ ዘመን
ሠራተኛ ወድቆ ሰነፍ ሲመሰገን ።
ትጥቅን አሳምሮ መልክን ማቅለጥለጥ
አጀብ እያበዙ ጭፍሮቹን ማስሮጥ
ሬት እያጠቆሩ ደሀን ማሸቆጥቆጥ ።
ጠጥቶ ማዛጋት ጠግቦ መሳለቅ
ተረትና ቧልታ ጨዋታ ማወቅ ።
መላስ እንዳመጣ በድፍረት መናገር
እንደ ሰስት ዓመት ልጅ ደርሶ መንቀባረር ።
እኔ የገሌ ልጅ ብሎ መዘናት
የምድረ በዳ አውሬ ገድሎ መቀባት
ጆብዱ እየቆጠሩ ፎከሮ መግባት ።
ከሙያ ተቆጥሮ ከትልቅ ቁም ነገር
ማዕረጉ ያገኙ ይሾሙበት ነበር ።
ኋላ ግን ውሎ አድሮ ዘመን ሲተላለፍ
ድንቁርና ሲያረጅ ሥልጣኑ ሲሸነፍ ።
በስንፍና ሕመም ደሙ ተመርዞ
በድንቁርና ሐብል እጁ ተገንዞ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜን እየፈጀ ሕይወትን መጨረስ
ሞት መሆኑን አውቆት አእምሮው ሲመለስ ።

በአርአያ ሥላሴ ለተፈጠረ ሰው
ኃይል የሚሰጥና ክብሩን የሚያድሰው ።

ትልቅ ዋጋ ያለው በውነት የሚከበር
ፍሬ የሚፈያሩ ከንደ ሙያ በቀር ።

ሌላው ሁሉ ከንቱ መሆኑ ታወቀ
እሱም በዚህ ዓለም እያንጸባረቀ
ይኖራል ዘላለም እንደ ተደነቀ ።

ካለም ነገር ሁሉ ዋጋው የበለጠ
እስከ አጥናፈ ምድር ዓለምን ያጌጠ ።

ለመሬት የሰጠ ውበትና ፀዳል
ክብርና ማዕርጉ ከሁሉ ይበልጣል ።

ያገኘውን ነገር በጁ ሲነካው
ሁሉን ያለመልኩ መልክ የሚሰጠው ።

በመሬት ያሳያል የጥበብ ታምር
በልጦና አሸንፎ ክብሮ የሚኖር ።

ሀብቱ ሁሉን በልጦ ከሁሉ ሲልቅ
ትሕትና ነው እንጂ ኩራት የማያውቅ ።

በድን የነበረው የማይላወስ
በሱ ነፍስ ዘርቶ የሚንቀሳቀስ ።

ያደነዘዘውን ሕመመ ስንፍና
ይመልስለታል ብርታትና ጤና ።



የሰፈረበትን እንቅፋት ጨለማ
ያጐናጽፈዋል የብርሃኑን ግርማ ።

ስሙ ምን ይባላል ብለህ ብትጠይቅ
ሥራ የሚባለው መሆኑን እወቅ ።

ባለቅኔው ሞልቶ ባገሩ ሲነዛ
መነዠሱው በርክቶ መናኙ ቢበዛ ።

እልፍ አእላፍ ቢሆን ጐበዙ ሲጠራ
ሀብታሙም ደሀውም ጥበብን ሊያፈራ
ሁሉ እኩል ተዋርዶ ትክክል ካልሠራ ።

መልካም ኑሮንና ሥልጣኔን ቢመኙ
የወህ ሽታ ነው መቸም አይገኙ ።

---

## ንግሥት አግሬፒና ።

ንግሥት አግሬፒና የኔሮን እናት
የተለየ ፍቅር ስላደረባት ።

ልጇዋን አለመጠን ትወደው ነበር
ብዙ ሊቃውንቶች ገብተው በምሥጢር ።

ልጅሽ እንቺን ገድሎ ይነግሣል የሚሉ
ክፉ ትንቢት አለ ተጠንቀቂ እያሉ ።

ሲመክሯት ይህ ትንቢት አልመስል ቢላት
ልጄ ይንገሥ እንጂ እኔ እንኳን ብሞት ።

www.ethiopianorthodox.org

ምንም ቅር አይለኝ እያለች ስትኖር
የተባለው ነገር ሳይሆን እንዳይቀር ።

ንግሩም እንዲደርስ ንግሥት አግሪፒና
በሕይወት ቆይታ ልጁዋም አደገና ።

ለብቻ እንደልቡ ደልቶት እንዲኖር
መንግሥቱን ከናቱ ቀምቶ ሊያስቀር ።

እሱዋንም ለመግደል ቍርጥ ሐሳብ አድርጎ
ከሎላልንቶቹ ጨካኙን ፈልጎ ።

ሒዶ እናቴን ግደል አለና ሰደደው
የተላከው ሎሌ ንጉሡ እንዲወደው ።

ሰተት ብሎ ገብቶ ከንግሥቲዋ ቤት
ራሱዋን በዱላ አንዴ እንደመታት
ያ ትንቢት መድረሱ ትዝ ስላላት ።

ራሴ ምን አጠፋ ሆዴን ምታው እንጂ
ጸንሶ የወለደ ኔሮን ብሎ ልጅ ።

አለችው ይባላል ምስኪኗ ንግሥት
እንደ እባብ በዱላ ተወግራ ስትሞት ።

## አ ን ቲ ስ ቴ ኔ ።

አንቲስቴኔ እሚባል የግሪክ ፈላስፋ
እውቀቱ የረቀቀ ትምህርቱ የሰፋ ።



ምግባራቸው ክፉ ስማቸው የጠፋ ።

የተጠሉ ሰዎች ሲያመሰግኑት
በጆሮው፡ ሰምቱዋቸው አዘነ በውነት ።

ሰው ሲያመሰግንህ እንዴት ታዝናለህ
መመስገንም ክፉ ነወይ ትላለህ ።

ብለው ቢጠይቁት ትልቁ አንቲስቴኔ
ዛሬ ምር ማዘን ይገባኛል እኔ ።

መመስገን መልካም ነው ምን ክፋት አለበት
ነገር ግን በልቤ አሁን ያዘንኩበት ።

እኔም እንደነሱ አንድ ክፉ ሥራ
አይተውኝ ይሆናል ምናልባት ስሠራ ።

እንጂ እኒህ ሰዎች ሌላ ምክንያት
እኔን ለማመስገን የሚችሉበት
ከወዴት አገኙ ብዬ በማለት
ራሴን መልሼ ተጠራጠርኩት ።

አለና መለሰ ትልቁ ፈላስፋ
ስለሚጠነቀቅ አመሉ እንዳይጠፋ ።

## ሊ ቅ ና ባ ል ተ ኛ ።

ማዕረግ አግኝቶ ክብሮ የሚኖር
የንጉሥ አጫዋች አንድ ሰው ነበር

www.ethiopianorthodox.org

በዚያው በሱ ዘመን ደህይቶ በጭንቅ
ተጉሳልቶ የሚኖር ነበረ አንድ ሊቅ ፡፡
የንጉሡ አሽከሮች ሊቁን ተናገረው
በምን ምክንያት ነው ወድቀህ የምትኖረው ፡፡
እኔ እንኳን ማይምኑ ምንም የማላውቅ
እስሩን ለፍልፌ ሰውን በማሳቅ ፡፡
ንጉሡ ወደውኝ ደልቶኝ እኖራለሁ
ክብርና ማዕርግ ሀብትም አገኝቻለሁ ፡፡
ይህንን ሰምቶ ሊቁ መለሰ እንዲህ ሲል
ጨዋታ የሚወድ አንተን ይመስል
ንጉሥ ስላገኘህ እውነት ደልቶሃል ፡፡
እኔም እንደዚሁ እግዚአብሔር ቢፈቅድ
እውቀት የሚፈልግ ጥበብ የሚወድ ፡፡
ንጉሥ አገኝና ለክብር እበቃለሁ
አለዚያም ጊዜዬን እንዲሁ እገፋለሁ ፡፡

---

## አ ሪ ስ ቶ ት ፡፡

አሪስቶት የሚባል ፈላስፋው መምህር
ከሊቆች መካከል ቆሞ ሲያስተምር ፡፡
የወዳጅን ነገር ጠቅሶ ሲነግራቸው
እንዲህ ሲል በምክሩ አስጠነቀቃቸው ፡፡



ስሙኝ ልንገራችሁ ወዳጆቼ ሆይ
ምንም ወዳጅ የለ በዚህ ዓለም ላይ ፡፡

. . . . . . . . . . . . . . . . .

ለዚሁ ላሪስቶት ለትልቁ ሊቅ
ወዳጆችህ ያንተን እውቀት በመናቅ ፡፡
ሲያሙህ ሰማናቸው ብለው ቢነግሩት
እንኳን ማማትና እሌለሁበት ፡፡
ቢደበድቡኝም አልቀየማቸው
አሚታ አይገሎዳኝም ሲል መለሰላቸው ፡፡
እኛም እንደ አሪስቶት ምንም ባንሆን ሊቅ ፡፡
ይገባናል ዘትር አሚታን መናቅ ፡፡

---

## ከፈላስፎች የተቀዱ ቃላት ፡፡

አጣሁ በለጡኝ ስል ለገንዘብ ለክብር
መማረሬ ቀርቶ ሕያው እግዚአብሔር ፡፡
እጅግ አርጎ ብዙ ደስ እያላት ነፍሴ
ስምህን ጠርት ማታ ይጠራል መላሴ
ፈጠርከሁ ስላልከኝ በአርአያ ሥላሴ ፡፡
ውለታን ካወቀ በውነት ሰውነቴ
በፊት ላመስግንህ በስነ ፍጥረቴ ፡፡

፨

www.ethiopianorthodox.org

ለሥጋ እንኳን ኑሮ አለው ብዙ ጣጣ
ሠርቶ እሚበላበት ሰው እንጀራ እያጣ ።
ደግሞ ነፍሴ በላይ እንዳትገላታ
ከሁሉ ጀምሮ ትገዛ ለጌታ ።

፨

የምድር ንጉሥ እንኳን ምሥጢር ያስጠብቃል
የሚያወራውም ሰው በብርቱ ይቀጣል ።
ሕያው ሥላሴማ ምሥጢሩ የሰፋ
ሲመራመሩበት ምነው አይከፋ ።

፨

የዚህ ዓለም ሰዎች ይቀባጥራሉ
የሰው ሥጋ መብላት እርም ነው እያሉ
እንግዲህ ወደፊት እንዳትታለሉ
የሰው ሥጋ ሆኗል መድኃኒት ለሁሉ ።

፨

ፀሐይ ብርሃንሽን የመልክሽን ፀዳል
ተመልክተው ሲያዩት በብዙ ማስተዋል
በጣም ይናፍቃል የፈጣሪሽ አምሳል ።

፨

ቆንጆ ጉብዝ ሀብታም አዋቂ ተብሎ
ያዳም ልጅ በመሬት እንደ አበባ በቅሎ ።
አንድ እንኳን ሳይታይ ከመካከል ተርፎ
ሁሉም ወዳቂ ነው እንደ አበባ ረግፎ ።

፨



ለሁሉ ጊዜ አለው ይላል ሰሎሞን
እጠይቀው ነበር በተገናኘን
ሞት የሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን ።

፨

የበረዶ ፍሬ ናት የኛ ሕይወት
ደመና ከሰማይ የወረወራት ።
ሥጋ ከለበሰ ሰው ዓለም ላይ መጥቶ
በረዶም ከሔደ ከደመና ወጥቶ
ወደ አፈር መግባቱ አይዘባም ከቶ ።

፨

ሰው ከናቱ ማሕጸን ሲወለድ ተረግዞ
በሞት ጐዳና ላይ ይጀምራል ጉዞ ።
ፊት ለፊት እያየው ትልቁን አደጋ
ልቡ ሲያፈገፍግ ሕይወቱ ሲጠጋ ።
ሲያውቀው በመሞቱ በጣም ይጨነቃል
መሸሽ በማጣት ቆሞ ይጠብቃል ።

※

አደገ ከበረ ነገሠ ገነነ
ተቀጨ ደኸየ ተሰዶ በነነ ።
አጣም በ ለጠገ ቸገረም ተመቸ
ሰው አመሰገነ አማ ጠላም ተቸ ።
ታደለ ዘበነ ተሾመ ታወቀ
ታረዘ ተጋዘ ተራበ ተናቀ ።

www.ethiopianorthodox.org

አንዱ ምን ጐድሎበት አንዱስ ምን ያተርፋል
ችግርና ተድላ ሁሉም እኩል ያልፋል
ሰው ሁሉ ትክክል ይሞታል ይረግፋል ።

※

ልቡናውን ውስጡን ራሱ መርምሮ
ኃጢአቱን ክፋቱን በሐሳቡ ሰፍሮ ።
ይህንን ሁሉ ዓመጽ የሌለው መጠን
አድራጊና ሠሪው እሱ መሆኑን ።
ሕሊናው ተረድቶት ሲያስበው መንፈሱ
ምን ፍጡር ይገኛል የማታፍር ነፍሱ
መልሶስ የማይንቅ ራሱን በራሱ ።

※

አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት
አምላክ አስወጣቸው ከምድረ ገነት ።
ሰው ረክሶ ቢገኝ እንደ እንሰሳ ሁሉ
ገሞራና ሰዶም እንደ ዕንቁጤት ከሰሉ ።
ኃጢአት በርክቶ መጠን ቢያጣ ክፋት
እግዚአብሔር በወሀ ዓለምን አጠፋት ።
ብዙዎቹ ነቢያት ሌት ተቀን ሳያርፉ
እስከ ጌታ ልደት ቃለ አብን ለፈፉ ።
አማኑኤል ወርዶ የሰው ሥጋ ለብሶ
ወንጌል አስተማረ አሪትን አድሶ ።



ይኸ ሁሉ ልፋት ሆኖና በከንቱ
በኃጢአትም ሆነ ባመጽ በክፋቱ
ብሶበታል እንጂ ስትመለከቱ
ምንም አልተሻለው ሰው ከሰውነቱ ።

※

ሰው በሥጋ በነፍስ ቆሞ በሕይወቱ
የሥጋን ደስታ ሲሆን ፍላጐቱ ።
ሊያገኛት አይችልም ከቶ ምን ቢሆን
ጨርሶ ካልጣለ የነፍሱን ወገን ።

※

ሁለት ነገር አለው ሰው ሲኖር ባለም ላይ
መልካም አመልና አንድ ክፉ ጠባይ ።
የሁለቱም ሥልጣን እያደር ይስፋፋል
ሰውም ባንዱ ለምዶ ባንደኛው ይጠፋል ።

※

ያለውን ማጥፋፋት ገብቶ በማይሆነው
ሁሉን ቅጥ ማሳጣት ለሷ ቁም ነገር ነው ።
የምትሔድበትን ሳታውቀው ጨርሳ
ዕውሩዋን የምትሮጥ እንዲያው በዳበሳ ።
ሳትፈራ ሳትሰጋ ሳታስተውል አስባ
እያቅነዘነዛት ገደል የምትገባ ።

www.ethiopianorthodox.org

አውቃላሁ ትላለች አውቀቷን በታችና
ክልፍልፍ ዕብድ ነች እመት ድንቁርና
የጥፋቷ ብዛት ልክ የለውምና ፡፡

፨

ብረትና ሸማ ቢጋጩ አንድነት
ከመከከላቸው አይወጣም ጩኸት ፡፡
ግን ብረት ለብረት አንድነት ቢማቱ
እርግጥ ነው ይገኛል ድምጥ ከሁለቱ ፡፡
ደንቆሮና አዋቂ አይስማሙም አሉ
እንደምን ይስማማ ሰው ያለመሰሉ ፡፡

※

ደግና ክፉውን እያደባለቀ
መንፈሱ ለይቶ ፍርድ ካላወቀ ፡፡
ድካሙ ከሆነ ለጌጡ ለልብሱ
ልፋቱ ከሆነ እስኪሞላ ከርሱ ፡፡
ካላቀረበለት ሕሊናው ወቀሳ
በምኑ ይበልጣል የሰው ልጅ ከእንስሳ ፡፡

※

አንዳንድ ሰው አለ መንፈሱ ደካማ
ደጋግመው ሲነግሩት ምንም የማይሰማ ፡፡
ዘርዝረው ሲያስረዱት አዳምጦ ጨርሶ
ጥያቄ ያመጣል እስር ተመልሶ ፡፡



የእውቀቱ መደንዘዝ ያሰነዋል ከቶ
ውሥጡን የሚሰራጭ በደም ሥሩ ሞልቶ
ቀዝቃዛ ወሀ ነው ደም መሆኑ ቀርቶ ፡፡

※

ገንዘብን ሰብስቦ የሚሰስትለት
የብረት ሳጥን ነው ሀብት የተመላበት
ከፍተው እንዳይወስዱ ቁልፉ የጠፋበት
ሀብቱም የሚገኘው የተሰበረ ለት ፡፡

※

ድካሙ ምኞቱ ሐሳቡ መንፈሱ
ልብና ሃይማኖት እምነትና ነፍሱ ፡፡
ከተቀላቀሉ ከገንዘቡ ጋራ
ፍቅር በሰው ልጅ ላይ ስሙም አይጠራ ፡፡

※

የተማረ ሆኖ እውቀቱን የማይገልጥ
ባለጠጋ ሆኖ ለደሀ የማይሰጥ ፡፡
ደሀ ሆኖ መሥራት የሚጠላ ልቡ
ሶስት ፍሬ ቢሶች ለምንም አይረቡ ፡፡

፨

ደሀ ሆኖ አመሉ ቁም ነገር ያለበት
ባንክ ኖት ይመስላል የተፈረመበት
ምን ዋጋ ባይኖረው የሚጠቀሙበት ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ትልቅ ሰው ተብሎ ምግባሩ ካልጠዳ
ስመ ቢስ ከሆነ አመለ ወራዳ ።
ወርቅ አንባር ይመስላል ቁሻሻና አፈር
ጥራጊ ጉድፍ ላይ ወድቆ የሚኖር ።

፨

ብዙዎቹ ተወልደው ከድህነት ቦታ
በኋላም አግኝተው ይሆኑና ጌታ
ቶሎ ይረሱታል የጧቱን ለማታ ።
እየተሳናቸው መለስ ብሎ ማየት
ማለዳ ሲነሡ የወጡበትን ቤት ።

፨

እንዳይነጋ እንዳይመሽ ብልሀት ተገኝቶ
ጊዜውን መከልከል እንዳይቻል ከቶ ።
እንዲሁም ባለም ላይ አለ ብዙ ነገር
በዚያም ቢሉት በዚህ መሆኑ የማይቀር ።

፨

ደስታና ኀዘን ውርጭና ፀሐይ
ሆነው ይመጣሉ በሰውነት ላይ ።
ሰው ደስ ባለው ጊዜ ኀዘኑን ይረሳል
ኀዘንም ሲያገኘው መጨነቅ ያበዛል ።
አስበ ሁለቱም አላፊ መሆኑን
ሲከፋው ደስታን ደስ ሲለው ኀዘኑን ።



አስቦ በመጠን ሁሉን የወሰነ
ብልህ ሰው ይባላል የተመሰገነ ።

፨

የሰው ገላ ለብሰን ሥጋን የመሰለ
ፍል ወሀ ሲነካው ቶሎ እየበሰለ ።
እንዴት ነጋም ጠባም ይጠጧል እሳት
አንዶ እሚቀቅል አልክል የሚሉት ።
ተገኘ ነውና ሰው ሁሉ ሳመሉ
ሰክራም ሲሰማኝ ይለኛል ወይ ጅሉ ።

፨

መጠጥና ሴቶች የዋሉበት ሥፍራ
ብዙ ሰው የፊጀ መሆኑ ነው ቄራ ።
የገባው ሰው ሁሉ እንደ ከብት ተነድቶ
አንዱም ሳይመለስ ቀረ ተበላሽቶ ።

፨

ከትንኮል አካሄድ ልቡናህ የጠራ
በማንም ላይ ቢሆን ክፉ የማትሠራ
መሆንህን አውቀኸው ሕሊናህ ሲኮራ ።
ያልደረስክበት ሰው እንዲያው በክፋት
ሊበድልህ ቢሻ በጠላትነት ።
ለእንደዚህ ያለ ጠብ መጨነቅህ ቀርቶ
ሕሊናህ ይታደስ በደስታ ሞልቶ ።

www.ethiopianorthodox.org

ያላንዳች ምክንያት የተነሣው ዲና
ከግዜር ትልቅ ጸጋ ሊያሰጥህ ነውና ።

※

ዓመጽና ወንጀል ዓድማም ሆነ ሴራ
ማንም ሰው አላየኝ ብለህ ስትሠራ ።
ለማቅረብ የሚችል ክስና ወቀሳ
እንድሺ ምስክር መ ኖሩን አትርሳ ።

჻

ቢያስቅም ቢያስለቅስ ቢገርምም ደስ ቢያሰኝ
ማነኛውም ይሁን አዲስ ነገር ሲገኝ ።
ዕጹብ ድንቅ እያለ ከዳር እስከ ዳር
ከጥንት የመጣ ነው ያለም መሸበር ።
ኋላ ግን ውሎ አድሮ ከርሞ በመሰንበት
ተረስቶ ይቀራል ሁሉም እንደዘበት ።

჻

ጋሬጣና አሽሟጣጭ አንድ ነው በሕሪያቸው
የሚያልፈውን ሁሉ በመቦጨቃቸው ።
ጋሬጣስ ቦጭቆም ያስቀራል በጥሶ
አሽሟጣጭ ክፉ ነው ይከተላል ነክሶ ።

჻

አጥፍቶ አሰዳቢ ዋሽቶ የሚረታ
ሰብሮ የሚያስከፍል ቀብጦ የሚያስመታ ።



ተማቶ የሚያስቅ ተሳድቦ እሚቆጣ
ተበድሮ አስከፋይ ሰርቆ የሚያሳጣ ።
አስቀይሞ አኩራፊ አስለቅሶ አዛኝ
በድሎ የሚከስ ቀምቶ ተለማኝ ።
የሚታዘዝለት ሰው ሁሉ እንደ ሎሌ
አለ በያለበት አንዳንድ አፈ ጮሌ ።

ጢስ ሳይኖረው እሳት ብቻውን አይነድም
እንዲያው ያለ ጥቅም ሰው አይዋደድም ።
ሰውን ሰው ሲወደው አንድ ጥቅም አለው
መሠረት አድርጎ የሚከታተለው ።

჻

ደስታና ኀዘን ተስፋና ፍራት
የሰውን ልጅ ዕድሜ ይዘው ያላባት
እየቆራረጡ ተከፋፈሏት ።

჻

ገና ነው እያሉ ካልሸፋፈኑት
እንደምን ያዩታል ሞትን ፊት ለፊት ።

჻

ሕይወት እንደ አራስ ልጅ ዕድሜዋን ስትገፋ
አወዛውዙኝ ባይ ነች እስክታንቀላፋ ።

჻

www.ethiopianorthodox.org

ሊከተል ይኖራል ነገር ሸሺውን
አሽከር ባለቤቱን ጠፊም አጥፊውን ።

፨

ራብ በሀል ያልፋል ጊዜ በተረት
ጭንቅ በሳቅ ይረሳል ፍቅርም በወረት ።

፨

ሐሳቡን ሰመመን ወስዶ እየመለሰው
ቆይቶ ይነቃል የተታለለ ሰው ።

፨

ስንፍናን የዘራ ችጋርን ዓጨደ
ሲታረድ ይስቃል ዋዛን የወደደ ።

፨

እጅግ ቢሸመግል ዓለም ምን ቢያረጅ
ይወዳል ጨዋታ እንደ ሕፃን ልጅ ።

ቢሰፈር ቢቆጠር ቢገመት ቢለካ
እምዩ ውለታሽ አያልቅም ወይ ለካ ።

፨

እየተደረበ ሁለት ሰው ባንድ አካል
አንደበቱ ሲምል ልቡናው ይከዳል ።

፨



ገንዘብ ሠርገኛ ነው ሰው ሲያቀርብ ሰብስቦ
ድኅነት ግን ሲያርቅ ይመስላል ተስቦ ።

※

ትምህርት ካልጨመረ በተፈጥሮ እውቀቱ
ሕፃን ልጅ ይሆናል ሰው ከነሽበቱ ።

※

በልቶ ማንቀላፋት ጠጥቶ መስከር
የሥራ ፊት ሙያ የሰነፍ ምግባር ።

※

ከሐቻምናም አምና ካምናውም ዘንድሮ
እያስጠላኝ ሔደ የዚህ ዓለም ኑሮ ።

※

የእግዚአብሔርን መኖር የሚክድ መንፈስ
ደን ያለ ሽፍታ ነው አዋጅ ለማፍረስ ።

※

እሙን ወዳጅ የለም ባሕርይን የመሰለ ፥
ይኖራል እስከ ሞት እንደተከተለ ።

※

አይገኝም ከቶ ቢፈልጉ ዘር
መስማት ከማይፈልግ የባሰ ደንቆሮ ።

※

ቢቈስልም ይድናል የተደበደበ
መላስ ግን ይኖራል እንዳንገበገበ ።

※

www.ethiopianorthodox.org

የሰው ነገር በዝቶ በሆዴ ውሥጥ ሞላ
ምን እንስሳ ልዋጥ ለቅሞ የሚበላ ።

※

አጊጦ ሲያምርበት እውቀት በትሕትና
ኩራት አስጠየፌ ለብሶ ድንቁርና ።

※

በሰው ልጅ ላይ ሳለ የቅናት በሽታ
ላንዱ ኀዘኑ ነው ያንደኛው ደስታ ።

※

ፈላስፋው ሲመክር አደራ ብሏል
በምትሠራው ነገር ቀስ ብለህ ቸኩል ።

※

ማዕርግ ለማግኘት ባለብዙ ክብር
ፀፊት ያስፈልጋል ተንቆ መኖር ።

※

ምን ውብ ነገር ቢሆን ከማድነቅ በፊት
ይገባል ጭራሹን ቀድሞ መመልከት

※



## የደሥታና የኀዘን ቅልቅልነት ።

ማን ሊያውቀው ይችላል
ያለምን ነገር
በጣም ይቸግራል ።
በሀሏን መናገር ።

ሰው ባለው ጉልበቱ ።
የለፋበት ሥራ ።
ይቀርና ከንቱ ።
ፍሬ ሳያፈራ ።

ተስፋውም ተቆርጦ ።
ኀዘን ሲጫነው ።
መጥናናትን መርጦ ።
ቢንቅ መልካም ነው ።

ልቡን በማጠንከር ።
መንፈሱ ሲጥናና ።
ተረስቶ የማይቀር ።
ኀዘን የለምና ።

ለቅሶና ደስታ ።
ሳቅና ኀዘን ።
ያልተለዩ መንታ ።
በሆኑበት ቀን ።

ታየች ልትሰወር ፣
ዓለም ተኽርኰርኵራ ።
የማይመረመር
ምሥጢር ልታፈራ ።

ደስታና ኀዘን ።
እየቀላቀልኩ ።
ልቤን ብዙ ዘመን ።
ስመግበው ኖርኩ ።

ከፋኝም ደስ አለኝ ።
ብዬ ለመመለስ ።
መለየት አቅቶኝ ።
እስኪ ሳንኝ ድረስ ።

ዓለም ሌባ ሆና ።
ፍጥረቱ አታላይ ።
በክፋት ጉዳና ።
ተስማሙበት ወይ?

ዓለም በዚህ መንገድ ።
ወደ ጽልመት ጥላ ።
በፍጥነት ስትሔድ ።
ዓየነው በመላ ።

www.ethiopianorthodox.org

አምራ እንደ ሠርገኛ ፡፡
ሊብሳ እየታየች ።
ሲቀርቧት ለቅሰኛ ።
ሆና ተገኘች ።

እንባ እያፈሰሰች ።
እንደ ዕሬት መራራ ።
ዓለም ታለቅሳለች ።
በሠራችው ሥራ ።

ምን አገኘሽ ብሎ ።
ለሚጠይቃት ።
ዓይኗ ኮከብ መስሎ ።
እንባዋም ውብት ።

ስስቅ ታለቅሳለች ።
ምነው ማለታችሁ ።
አይችልም ትላለች ።
መለየት ዓይናችሁ ።

ዓለምን መውቀሱ ።
ይቅርብን ተነቅኗል ።
ሰው ሲስቅ ማልቀሱ ።
መሆኑ ተጽኗል ።

## ሁለት መላጦች ።

ሁለት በራ ሰዎች ሲያልፉ በጐዳና
ዕቃ መሬት ወድቆ ብልጭ ሲል ዓዩና ።
ተሽቀዳድመው ሔደው ከቦታው ሲደርሱ
ተፎካከሩበት ሁለቱም ሊያነሱ ።
በኋላም ተማትተው በጥፊ በጡጫ
አንደኛው ነጠቀ በጉልበቱ ብልጫ ።



አገላበጠና ቢመለከት ፈጥኖ
ዕቃውን አገኘው ማበጠሪያ ሆኖ ።
እስኪ ሁላችሁም በሉ ፍረዱት
እሱ ራሱ በራ ጠጉር የለበት ።
ሮጦ ተማትቶ ቀምቶ ቢያመጣ
ምን ያደርግለታል ሚዶ ለመላጣ ።
ሰዎች ይፋጃሉ አስበው ሳይፈርዱ
የተጣሉበትን ጥቅሙን ሳይረዱ ፡
ከመጣላት በፊት ከመቀያየም
የነገሩን ፍሬ መረዳት መልካም ።

## ለጸፊዎችና ለፈላስፎች ምሥጋና ።

የትምህርቱ እርሻ እጅግ በጣም ሰፊ
ሁዳዱ መጽሐፍ ነው ገበሬውም ጻፊ ።
ሐሳብ ከሚባለው ከትልቅ ጐተራ
ብዕር እጅ ሆኖ ጨብጦ እየዘራ ።
የቀለሙም ፍሬ አብቦ እያፈራ
ለምልሞ ተገኘ ይህ መልካም አዝመራ ።
እንዲህ ያለ አዝመራ እውነትም ትልቅ
ቢመረት ቢመረት ሰብሉ የማያልቅ ።

www.ethiopianorthodox.org

ታሪክሽ ማማሩ ።
አንች የንጋት ኮከብ ።
ዝናውና ክብሩ ።
ተሰምቶ አይጠገብ ።

ማዕበል ተነሥቶ ።
ዓለም ሲናወጥ ።
ሽብሩ በርክቶ ።
ፍጡር ሲራወጥ ።

እጅሽን ዘርጊልኝ ።
አንቺ ሁኚኝ ተስፋ ፣
ሞት እንዳያገኘኝ ።
ጨርሼ እንዳልጠፋ ።

የለመነሽ በእውነት ።
እምነቱ እየጠና ።
ሰውነቱን መቅሠፍት ።
አይነካውምና ።

እግዜር ላገሩችን ።
ቃል ኪዳን ሲገባ ።
ለኢትዮጵያ እናታችን ።
ሆንሻት ባልደረባ ።

ክፉ ቀን ሲመጣ ።
መዓት እየዘራ ።
ከሰዓቱ ቁጣ ።
ሰውሪያት አደራ ።

የሃይማኖት ፀዳል ።
የሰማይ ንግሥት ።
የርኅራኄ አምሳል ።
የዓለም መድኃኒት

ጠላት በመጣ ቀን ።
ደግሞ እንዳትጠቃ ።
ቆመሽ ከሷ ወገን
ሁኝላት ጠበቃ ።

ተፈጸመ ።

የምንባብ ማውጫ ።


| ድርሰት ። | ገጽ ። |
|---|---|
| አንድ አምላክ | ፯ |
| የሰው ሐሳብ | ፲ |
| ዓለምና ጊዜ | ፲፩ |
| የሰው ዕድል | ፲፫ |
| የሰው ጠባይ | ፲፯ |
| የግፈኞች ፍርድ | ፳፩ |
| አባት ልጅ አህያ | ፳፫ |
| ደግነትና ክፋት | ፳፱ |
| ምሥጢርና ወሬ | ፴ |
| በዓመጽ የመጣ ገንዘብ | ፴፬ |
| የሁብት ትዕቢት | ፴፮ |
| የክፋት ተጋብአኖት | ፴፯ |
| ሁለት ወንድማማቾች | ፴፰ |
| ጥበብ | ፵፩ |
| ሰውና ታሪክ | ፵፫ |
| ሕይወት እንቅልፍ ነች | ፵፮ |
| ባልና ሚስት | ፵፰ |
| አንበሳና ጦጣ | ፶ |


www.ethiopianorthodox.org

እውቀትና ክፋት ፶፪
አይጥና ድመት ፶፫
ሥራ ፶፬
ንግሥት አግሪፒና ፶፯
አንቲስቴኔ ፶፰
ሊቅና ባለተኛ ፶፱
አሪስቶት ፷
ከፈላስፎች የተቀዱ ቃላት ፷፩
የደስታና የሀዘን ቅልቅልነት ፸፫
ሁለት መላጦች ፸፮
ለጸሐፊዎችና ለፈላስፎች ምሥጋና ፸፯
ለእመቤታችን ምሥጋና ፸፱